## የጨረታ ማስታወቂያ
## ቁጥር HU-ONT-06-2008

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ካምፓስ የአካዳሚክ ሕንፃ ፈርኒቸሮች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ሕጋዊ ብቃት ያላቸውን የአገር ውስጥ ተጫራቾች ይጋብዛል። በዚህ ጨረታ መሳተፍ የሚፈልጉ፦

1. የጨረታ ሰነዱን ከዚህ በታች ከተጠቀሱት አድራሻዎች የማይመለስ ብር 150.00 (አንድ መቶ አምሳ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ።
2. ዋጋቸውን በመሙላትና በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ እስከ መስከረም 11 ቀን 2008 ዓ.ም. ከጧቱ 4:00 ከታች በተጠቀሱት አድራሻዎች በተዘጋጀው የጨረታ ሣጥን ማስገባት ይኖርባቸዋል።
3. የጨረታ ሣጥኑ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዚሁ ዕለት ከጧቱ 4:00 ላይ ከታች በተጠቀሱት አድራሻዎች ይከፈታል።
4. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የጨረታ ሰነድ ጋር አካተው ማቅረብ ያለባቸው ሰነዶች፦
    - 4.1. በዘርፉ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸውና ለዘመኑ ለመታደሱ ማረጋገጫ፤
    - 4.2. ማንኛውንም የወቅቱን የመንግሥት ገቢ ግብር ለመክፈላቸው ወይም ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣታቸው ማረጋገጫ፤
    - 4.3. በመንግሥት ጨረታዎች ለመሳተፍ የሚያስችል ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አግባብ ካለው ሕጋዊ አካል፤
    - 4.4. ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ለመሆናቸው የሚያረጋግጥ የምዝገባ ምስክር ወረቀት አግባብ ካለው ሕጋዊ አካል፤
    - 4.5. የጨረታ ማስከበሪያ ብር 50,000.00 (አምሳ ሺህ ብር) በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም ሲፒኦ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
5. ተጫራቾች የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ካምፓስ የአካዳሚክ ሕንፃ ፈርኒቸሮች ማስረከቢያ ቦታ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ መሆኑን ማወቅ አለባቸው።
6. አሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ያሸነፉበትን የጠቅላላ ዋጋውን 10% (አሥር በመቶ) የሥራ አፈፃፀም ዋስትና በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርባቸዋል።
7. ተጫራቾች ዋጋ በሚያቀርቡበት ጊዜ የጫኝና አውራጅ ክፍያና ተያያዥ ወጪዎችን በማካተት ማቅረብ አለባቸው።
8. ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
9. ለተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ መጠየቅ ይቻላል።

| | |
|---|---|
| ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ማዕከላዊ ግዥ ንዑስ<br>የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 002<br>ስልክ ቁጥር 0255530016/0255530349<br>ፋክስ ቁጥር 0255530300/354/325<br>ሐረማያ | አዲስ አበባ አራት ኪሎ ሮሚና ካፌ<br>አጠገብ አንደኛ ፎቅ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ<br>ጉዳይ አስፈፃሚ ቢሮ ቁጥር 15<br>ስልክ ቁጥር 0111571847/0915747077<br>አዲስ አበባ |



የማዕከላዊ የግዥ ንዑስ
የሥራ ሂደት ቡድን
Central Procurement